# ልጆችን ከኩፍኝ ስለመጠበቅ የሚጠየቁ የተለመዱ ጥያቄዎች

## ስለ ኩፍኝ የሚነሱ ጥያቄዎች

### ኩፍኝ ሊያሳምምዎ ይችላል?

አዎ። ኩፍኝ በጣም ከባድ ሊሆን የሚችል ሲሆን ሞትን ጨምሮ ከባድ ችግሮችን ሊያስከትል ይችላል። ለምሳሌ፣ ከ5 ክትባት ያልተከተቡ በኩፍኝ የተያዙ ሕፃናት ውስጥ 1 ወደ ሆስፒታል መሄድ አለባቸው፣ ከ20 ውስጥ 1 የሳንባ ምች ሊይዛቸው ይችላል፣ እና ከ1,000 ውስጥ 1 ለሕይወት አስጊ የሆነ አእምሮ እብጠት ያጋጥማቸዋል።

### የኩፍኝ ምልክቶች ምንድናቸው?

የኩፍኝ ምልክቶች ብዙውን ጊዜ ከተጋለጡ በኋላ ከ7 እስከ 14 ቀናት ውስጥ ይታያሉ። የተለመዱ ምልክቶች ከፍተኛ ትኩሳት፣ ሳል፣ የአፍንጫ ፍሳሽ፣ ሽፍታ እና የአይን መቅላት እና እምባ መቋጠር ናቸው። በኩፍኝ የሚመጣ ሽፍታ አብዛኛውን ጊዜ የሚጀምረው ትኩሳቱ ከጀመረ ከጥቂት ቀናት በኋላ ሲሆን መጀመሪያ ላይ ፊት ላይ ይታያል እና ወደ ታች ይሰራጫል።

### አንድ ሰው ኩፍኝ ቢይዘው፣ ሕክምና ማግኘት ይችላል?

ለኩፍኝ ምንም አይነት የተለየ ሕክምና ወይም መድኃኒት የለም። የሕክምና እንክብካቤው የሚያተኩረው ምልክቶችን በማስታገስ እና ደጋፊ እንክብካቤን በማመቻቸት ላይ ነው። ልጅዎን ከኩፍኝ በሽታ ለመጠበቅ በጣም ጥሩው መንገድ የMMR (ኩፍኝ ፣ የጆሮ ደግፍ፣ ሩቤላ) ክትባት ማግኘታቸውን በማረጋገጥ ነው።

### ልጄ ለኩፍኝ ተጋልጦ ይሆናል ብዬ ካሰብኩ ምን ማድረግ አለብኝ?

ልጅዎ ለኩፍኝ ተጋልጦ ሊሆን እንደሚችል የሚነግርዎት የስልክ ጥሪ ከጤና መምሪያው ሊደወልልዎ ይችላል። ከጤና መምሪያው የተሰጡ መመሪያዎችን ይከተሉ። ልጅዎ የኩፍኝ ምልክቶችን ማሳየት ከጀመሩ፣ ቀጥሎ ምን ማድረግ እንዳለብዎት እንዲነግርዎት ወዲያውኑ ወደ ዶክተራቸው ወይም ወደ ሆስፒታል ይደውሉ። ደህንነቱ የተጠበቀ ጉብኝት ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ከመድረስዎ በፊት ይደውሉ።

## ስለ MMR ክትባት የሚነሱ ጥያቄዎች

### የMMR ክትባት ደህንነቱ የተጠበቀ ነው? እንዴት እናውቃለን?

አዎ። ከ50 ዓመታት በፊት ፈቃድ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ልጆች የMMR ክትባትን ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ወስደዋል። Centers for Disease Control and Prevention (CDC፣ የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማዕከላት) እና The U.S. Food and Drug Administration (FDA፣ የምግብ እና የመድኃኒት አስተዳደር) ክትባቶች ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆናቸውን ያለማቋረጥ ለመከታተል እና ለማረጋገጥ በርካታ የደህንነት ስርዓቶችን ይጠቀማሉ። MMR በዓለም አቀፍ ደረጃ ደህንነቱ የተጠበቀ ስለመሆኑ ተፈትኗል።

### የMMR ክትባት የጎንዮሽ ጉዳቶች ወይም አደጋዎች ምንድናቸው?

ልጅዎ የMMR ክትባት ከወሰደ በኋላ፣ እንደ ክትባቱ በተሰጠበት ቦታ ላይ ህመም፣ ትኩሳት ወይም ሽፍታ ያሉ መለስተኛ የጎንዮሽ ጉዳቶች ሊያጋጥሙት ይችላሉ። እነዚህ አብዛኛውን ጊዜ የሚቆዩት ለጥቂት ቀናት ብቻ ሲሆን በራሳቸው ይጠፋሉ። የበለጠ ከባድ የጎንዮሽ ጉዳቶች እምብዛም አይደሉም፣ ነገር ግን ለሚጥል በሽታ መሰል መንቀጥቀጥን ሊያስከትል የሚችል ከፍተኛ ትኩሳትን ሊያካትቱ ይችላሉ። የሚጥል በሽታ መሰል መንቀጥቀጦች በአጠቃላይ ምንም አይነት ዘላቂ ጉዳት እንደማያስከትሉ ወይም ዘላቂ ተጽዕኖዎችን እንደማያስከትሉ አይቆጠርም።

### ከMMR ክትባት በኋላ የረጅም ጊዜ አደጋዎች አሉ?

የMMR ክትባትን በተመለከተ የብዙ አስርተ ዓመታት ልምድ አለን፤ የረጅም ጊዜ ጉዳት እንደሚያደርስ የሚያሳይ ምንም ማስረጃ የለም።

### እንደ MMR ያሉ ክትባቶች ኦቲዝም ያስከትላሉ?

በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሕፃናትን ያካተተ ሰፊ ጥናት ተደርጓል፤ ይህም በክትባት እና በኦቲዝም መካከል ምንም ግንኙነት እንደሌለ ያሳያል።

---

**ስለ የልጅነት ክትባቶች የበለጠ ይወቁ፡-**

ስለ ኩፍኝ የሚነሱ ጥያቄዎች

**cdc.gov/measles/about/questions.html**

ስለ ልጆችዎ ክትባቶች

**cdc.gov/vaccines -children/about/index.html**

## ስለ MMR ክትባት የሚነሱ ጥያቄዎች

### የMMR ክትባቶች ምን ያህል በጥሩ ሁኔታ ይሰራሉ?

የMMR ክትባት በጣም ጥሩ በሆነ ሁኔታ ይሰራል። ክትባቱ ሁለት ጊዜ ከተወሰደ በኋላ 97% የሚሆኑ ሰዎችን ከኩፍኝ ይጠብቃል። የተከተቡ ሰዎች ኩፍኝ የመያዝ እድላቸው በጣም አነስተኛ ነው፣ ነገር ግን ሊከሰት ይችላል። ይሁን እንጂ በሽታውን ወደ ሌሎች የማሰራጨት እድላቸው አነስተኛ ነው። በተጨማሪም በተለምዶ ቀለል ያለ ህመም እና አነስተኛ ችግሮች ያጋጥሟቸዋል።

### ልጆቼን ካላስከተብኩ፣ በእርግጠኝነት ለኩፍኝ በሽታ የመጋለጥ እድላቸው ከፍተኛ ነው?

ኩፍኝ በቀላሉ የሚተላለፍ ሲሆን በዓለም ላይ ካሉት በጣም ተላላፊ በሽታዎች አንዱ ነው። ከኩፍኝ በሽታ ጥበቃ ያልተደረገለት ማንኛውም ሰው አደጋ ላይ ነው። የጉዞ መጠን እየጨመረ በመምጣቱ እና የክትባት መጠኑ እየቀነሰ በመምጣቱ፣ የኩፍኝ ጉዳዮች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱን ያስተዋልን ሲሆን ይህም የMMR ክትባትን ይበልጥ አስፈላጊ ያደርገዋል።

### ቤተሰባችን ዓለም አቀፍ ጉዞ ለማድረግ እያቀደ ነው። ልጃችንን ከኩፍኝ እንዴት መጠበቅ እንችላለን?

ዓለም አቀፍ ጉዞ ከመጀመርዎ በፊት፣ በቤተሰብዎ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ሰው በMMR ክትባት ከኩፍኝ በሽታ ራሳቸውን መከላከል ያለባቸው ሲሆን የዚህም ምክንያቱ የኩፍኝ ወረርሽኝ በዓለም ዙሪያ ይከሰታል። እነዚህ ምክሮች ከ6-11 ወር እድሜ ላላቸው ጨቅላ ህጻናት የMMR መድሃኒት መጠን እና ከ12 ወር እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ህጻናት፣ ለታዳጊዎች እና አስቀድመው ክትባት ላልወሰዱ አዋቂዎች ሁለት የመድሃኒት መጠኖችን (በ28 ቀናት የተለዩ) ያካትታሉ። ከጉዞው ቢያንስ ከ2 ሳምንት በፊት ክትባት መውሰድ ከኩፍኝ በሽታ በጣም ጥሩ የሆነ መከላከያ ይሰጣል።

### ህፃናት ሲወለዱ ለኩፍኝ በሽታ የመከላከል አቅም አላቸው?

አንድ ሕፃን የኩፍኝ በሽታ የመከላከል አቅም ካላት እናት ሲወለድ፣ ከእናቷ ፀረ እንግዳ አካላት የተወሰነ ጥበቃ ያገኛል፦ ይህ ጥበቃ በህይወት የመጀመሪያዎቹ ወራት ውስጥ ይረዳል፣ ነገር ግን ከጊዜ በኋላ ቀስ በቀስ ይዳከማል። እንደ MMR ክትባት ያሉ ክትባቶች ልጅዎ የኩፍኝ በሽታ የመያዝ አደጋ ሳይኖርበት የመከላከል አቅም እንዲያዳብር ለመርዳት አስተማማኝ መንገድ ናቸው።

### ህፃናት ገና በለጋ እድሜያቸው የMMR ክትባት መውሰድ ያለባቸው ለምንድን ነው?

ጭቅላ ህጻናት እና ልጆች እንደ ኩፍኝ ላሉ ከባድ በሽታዎች ከመጋለጣቸው በፊት ለመከላከል ክትባቶችን በለጋ እድሜያቸው እንዲከተቡ ይመከራል። ልጆች የመጀመሪያውን የMMR ክትባት ከ12-15 ወራት ውስጥ በመደበኛነት የሚከተቡ ሲሆን የዚህም ምክንያቱ ከእናታቸው የተቀቀበሏቸው ፀረ እንግዳ አካላት የመከላከል ችሎታ የሚጠፋው በዚህ ጊዜ ስለሆነ ነው። በዚያ ዕድሜ ላይ፣ በኩፍኝ በሽታ የተያዙ ልጆች ለከባድ ችግሮች የመጋለጥ እድላቸው ከፍተኛ ነው።

### በአንድ ጊዜ ብዙ ክትባቶችን በመውሰድ የሕፃናት ሰውነት ከአቅሙ በላይ ሊሆንበት ይችላል?

አይ፣ ጤናማ ሕፃናት በየቀኑ በሺዎች የሚቆጠሩ ጀርሞችን ይዋጋሉ። ክትባቶች አንቲጂኖችን ይጠቀማሉ፤ እነዚህም የሰውነት በሽታ የመከላከል ስርዓት በሽታዎችን የሚዋጉ ፀረ እንግዳ አካላትን እንዲገነባ የሚያደርጉ የጀርሞች ክፍሎች ናቸው። ሕፃናት በአንድ ቀን ውስጥ በርካታ ክትባቶችን ቢወስዱም፣ ክትባቶች ህጻናት በየቀኑ በአካባቢያቸው የሚያጋጥሟቸውን አንቲጂኖች በጣም ትንሽ ክፍል ብቻ ይይዛሉ።

### ልጄ አሁን ታሟል። ዛሬም ቢሆን ክትባቶችን መውሰድ ችግር አለው?

ስለ ልጅዎ ህመም ይንገሩኝ። መቼ ጀመረ እና ምልክቶቹ ምንድን ናቸው? ብዙውን ጊዜ፣ ልጆች እንደ ጉንፋን፣ የጆሮ ህመም፣ መለስተኛ ትኩሳት ወይም ተቅማጥ ያሉ ቀላል በሽታዎች ቢኖሩባቸውም እንኳ ክትባት ሊወስዱ ይችላሉ። ልጅዎ ቀላል ሕመም ካለባቸው ክትባት ለመውሰድ መጠበቅ ምንም ዓይነት የጤና ጥቅም እንደሌለው ያስታውሱ። ልጆች ከከባድ በሽታዎች እንዲጠበቁ ክትባታቸውን በጊዜ ማግኘታቸው አስፈላጊ ነው።

---

**ስለ የልጅነት ክትባቶች የበለጠ ይወቁ፦**

**ስለ ኩፍኝ የሚነሱ ጥያቄዎች**

**cdc.gov/measles/about/questions.html**

**ስለ ልጅዎ ክትባቶች**

**cdc.gov/vaccines - children/about/index.html**